# <u>ሁሌም ማለዳ</u>

ሁሌም ማለዳ አዲስ ነው እግዚአብሔር
የሚሳነውም የለም ምንም ነገር
እጹብና ድንቅ ተአምር የሚሰራ
ቅዱስ እግዚአብሔር ሆነ ከእኛ ጋራ

የእኛ ክንድ ያልቻለውን የእርሱ ክንድ ይችለ
ተራራውን ንዶ ይደለድለዋል
ግፈኞች ቢገፉንም ወደ እርሱ እንጠጋለን
በሚመቸው ክንዱ እንደገፋለን

አዝ...

አይኑ እንቅልፍ የለውም ሕዝቡን ሲጠብቅ
ልብን ኩላሊትን ምስጢርን የሚያውቅ
የብርሃን ድንኳን በሰማያት ተክሎ
ሲጠራን ይውላል ኑ ወደ እኔ ብሎ

አዝ...

በወደደን በእርሱ ከሁሉ እንበልጣለን
የማይቻለውን በእርሱ እንችላለን
በኃይለ መንፈሱ ድካማችን ጠፍቶ
ከፊቱ ያቆመናል ደግፎ አበርትቶ

አዝ...

የሚገዳደሩን ሺ ሆነው ቢነሱ
እንደጉም በነኑ ስንጮህ ወደ እርሱ
ለካስ ሁሉም ያልፋል እግዚአብሔር ሲነሳ
መጽናናት ይሠጣል ሀዘን የሚያስረሳ

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org